May 20,2014

# እገሠግሣለሁ

1.ነፍሴ አንተን ተጠማች (መዝ 63፡1)

2.ሳበን ካንተም በኋላ እንሮጣለን (መኃልይ 1፡4)

3.ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች (መዝ 63፡5)

ጸሎት ወደ ውስጠኛው የእግዚአብሔር ማደሪያ የሚደረግ ግሥገሣ እንደ ሆነ መዝ 63፡1 «አምላኬ አምላኬ ወደ አንተ እገሠግሣለሁ» የሚለው ቃል ያመለክተናል፡፡ጉዞ መነሻ እንዳለው ሁሉ ጸሎታችንም ከውጨኛው አደባባይ ወደ ቅድስት ከዚያም ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ያነጣጠረ ነው፡፡ ዳዊት «ኃይልህንና ክብርህን አይ ዘንድ እንዲሁ በመቅደስህ ውስጥ ተመለከትሁ»(መዝ 63፡2) የሚለንም ለዚህ ነው፤ጸሎት ደረጃዎች እንዳሉት ሲያመለክተን፡፡በዚህ ቃል መሠረት የምንረዳው ነገር ጸሎታችን እየጠለቀ በሄደ ቁጥር የእግዚአብሔርን  ኃይልህንና ክብሩን የማየት በረከታችን እየጨመረ እንደሚሄድ ነው፡፡ለዚህ ነው በግልብ(superficial) ጸሎት «ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች»(መዝ 63፡5) ማለት የማንችለው፤ውስጠኛው አደባባይ ውስጥ ሳንውል ሳናድር!

«እገሠግሣለሁ»(መዝ 63፡1) ስንል የጸሎት እርምጃችን ጽናት፣ትግዕስት፣ንቁነት፣እምነት ወዘተ እንደ ግብዓት እንደሚያስፈልጉት መገንዘብ አለብን፡፡ትኩረታችንም እርሱ ላይም መሆን አለበት፡፡ብዙ ጊዜ ለጸሎት ስንደረደርና ለመገሥገሥ ስናስብ «ነፍሴ አንተን ተጠማች፤ሥጋዬ አንተን እንዴት ናፈቀች»(መዝ 63፡1)የሚል መንፈስን ይዘን ነው የምንቀርበው፤ተግዳሮቶቻችን እያሰብን፤ህመማችን እያሰብን፤ፈተናዎቻችን እያሰብን፣መከራዎቻችን እያሰብን ወዘተ፡፡ባለፉ ጊዜያት በነበሩን የጸሎት ጊዜያት የነበሩንን ወርቃማ ልምምዶች እያሰብንም አምላካችን አሁንም እንዲደግመው በመማጸን በፊቱ እንሆናለን፡፡

ጸሎትን ስንጀምር የመጸለይ ፍላጎታችን እጅግ ዝቅ ያለ ስለሚሆን ቶሎ ለማቋረጥ እንፈተናለን፡፡ድካም ይጫጫነናል፤አእምሮአችን ይበታተናል ሌላም ሌላም፡፡ከተወሰነ መቃተትና ጽናት በኋላ የእግዚአብሔር ህልውና የሚታወቀን ደረጃ ውስጥ እንገባለን፡፡በዚህ ደረጃ ላይ ሆነን ነው «ነፍሴ በኋላህ ተከታተለች»(መዝ 63፡8) የምንለው፡፡በዚህ ደረጃ ላይ ሆነን ነው «ሳበን ካንተም በኋላ እንሮጣለን.....ከወይን ጠጅ ይልቅ ፍቅርህን እናስባለን»(መኃልይ 1፡4) የምንለው፡፡ትንሽ ትንሽ ዝማሬና ምስጋና ያምረናል፡፡ጸሎታችን ሳናቋርጥ መቀጠል ያምረናል፡፡ይህ ደረጃ ባብዛኛው ሁለተኛው የጸሎት ደረጃ ነው፡፡ይህ ደረጃ  እንደ ግለሰቡ የጸሎት ሕይወት እስከ አንድ ሰዓት ሊፈጅ ይችላል፡፡በሚገባ የጸለዩ ስለሚመስላቸው ብዙ ሰዎች እዚህ ደረጃ ላይ ያቋርጣሉ፡፡እንዳውም ስለነበራቸው ድንቅ የጸሎት ጊዜም ለሰዎች ሊመሰክሩም ይችላሉ ፡፡ይህንን ደረጃ ስናልፍ ሦስተኛው ደረጃ ውስጥ እንገባለን፡፡

ሦስተኛው የጸሎት ደረጃ ከጌታ ጋር እጅግ አስደናቂ ህብረት የምናደርግበት የጸሎት ደረጃ ሲሆን እውነተኛ የሕይወት ለውጥ(transformation) ለማየት መልካም ዕድሎችን ይፈጥርልናል፡፡በዚህ የጸሎት ደረጃ ላይ አዘውትረን ስናሳልፍ ነው «ነፍሴ በቅቤና በስብ እንደሚጠግቡ ትጠግባለች፤ከንፈሮቼም ስምህን በደስታ ያመሰግናሉ»(መዝ 63፡5)ብለን በእውነት እና በድፍረት መናገር የምንችለው፡፡እዚህ ደረጃ ውስጥ ዝምታ ይበዛል፡፡«መንፈስ ራሱ በማይነገር መቃተት የሚማልድበት»(ሮሜ 8፡27) የጸሎት ደረጃ ነው፤እንደ እግዚአብሔር ፈቃድም እንጸልያለን፡፡እንባ ቋንቋችን ይሆናል፡፡እውነተኛ ንሥሓ እንገባለን፡፡ከጌታ ጋር ለመራመድ እንስማማለን፡፡ከራስ ወዳድነት የፀዱ ጸሎቶችን እንጸልያለን፡፡የእግዚአብሔር ጸጋ በሕይወታችን ስለሚጨምር የፍቅር ሰዎች እንሆናለን፡፡ግብዝነት ከሕይወታችን ይወገዳል..............

ጌታ ሆይ እባክህ አስበን !! ወደ ጠለቀ ጸሎት ሳበን!


በቀለ በላቸው(ዶ/ር)

Beke_abay@yahoo.com

240-330-5004